የሰ/መ/ቁ. 54326

ኀዳር 03 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ሓጐስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አንበሳ ጫማ አ/ማህበር -የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ እትሁን አያሌው - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96"ን" መሰረት አድርጐ የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በምእራብ አማራ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- ከአመልካች ጋር የግል ስራ ክርክር ሲያደርጉ ከቆዩ በሁዋላ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም በሰ/መ/ቁ. 44515 የቅጥር ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው በማለት ውሳኔ ከሰጠ በሁዋላ ታህሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 11/መ/485/2-3 በተፃፈ ደብዳቤ ከባህር ዳር ሽያጭ መደብር ወደ ሃዋሳ ሽያጭ መደብር ያለበቂ ምክንያት ያዛወራቸው መሆኑን በመግለጽ ዝውውሩ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ክሱ የግል የስራ ክርክር በመሆኑ በቋሚ ቦርድ ሊታይ የማይገባው መሆኑን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ የተከራከሩ ሲሆን ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ግን ድርጅቱ ዝውውሩን ለማድረግ የወሰነው ድርጅቱ ያለበት ቦታ ለኢንቨስትመንት የተሰጠ በመሆኑ በህብረት ስምምነቱ መሰረት መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ቋሚ ቦርድም ጉዳዩን መርምሮ ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጪ የተፈፀመ መሆኑን በማረጋገጥ ዝውውሩ ተገቢ አይደለም በማለት ሰርዞታል፡፡ ይህ ውሳኔ በየደረጃው ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሳኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ድርጅት ወኪል መጋቢት 20 ቀን 2002 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሚል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ቦርዱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን አይችልም፣ዝውውሩም የተከናወነው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት ነው የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር ውሳኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ

ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪ ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ ተደርጕአል፡፡ በዚህም መሰረት ተጠሪ ቀርበው የፁሁፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ላይ የግል የስራ ክርክር አቅርበው በዚህ ሰበር ችሎት ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠረች ሰራተኛ ነች ተብሎ ውሳኔ ጥቅምት 25 ቀን 2005 ዓ.ም ተሰጥቶ አመልካች ድርጅት ታህሣሥ 16 ቀን 2002 ዓ.ም ዝውውሩን መፈፀሙን፣ ዝውውሩን ለመፈፀም አመልካች በምክንያትነት የጠቀሰው ድርጅቱ ያለበት ቦታ ለኢንቨስትመንት በመፈለጉ ቦታውን እንዲለቅ ከሚመለከተው አካል ትእዛዝ የደረሰው መሆኑን፣ሆኖም ዝውውሩ በሁሉም ሰራተኛ የተከናወነ ሳይሆን በተጠሪ ላይ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ቋሚ ቦርድም ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሰረት የተደረገ ሳይሆን ከሕጋዊ ምክንያቶች ውጪ መከናወኑን በፍሬ ነገር ደረጃ ማረጋገጡን ከቦርዱ ውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ፍሬ ነገርን ለማጣራትና ማስረጃን ለመመዘን ስልጣን ያላቸው ቦርድና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ዝውውሩ በህብረት ስምምነቱ ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጪ ስለመፈፀሙ በፍሬ ነገር ደረጃ የተስማሙበት ከሆነ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ ምዘና እንጂ የሕግ ትርጉም ጥያቄ አይደለም፡፡ ፍሬ ነገርና ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ደግሞ የዚህ ሰበር ችሎት ሥልጣን አለመሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ) እና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው የተባለው ተጠሪ ከአመልካች ላይ የነበራቸው ክስና ከዚህ በሁዋላ የተከናወኑትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፤ማስረጃዎቹም ተመዝነው በመሆኑ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ እና በዚህ ችሎት ሊታይ የሚችል ሁኖ አላገኘውም፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በጉዳዩ ላይ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 06880 መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም የቦርዱን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ